የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ– ታህሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 25
ADDIS ABABA - 15th December, 1998


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፻፵፭/፲፱፻፺፩ ዓ.ም
ብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ...................................................... ገጽ ፱፻፴፩


## CONTENTS


Proclamation No. 145/1998
The National Fertilizer Industry Agency Establishment (Amendment) Proclamation ............ Page 931


### አዋጅ ቁጥር ፻፵፭/፲፱፻፺፩
### ብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅን እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፻፵፭/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ማሻሻያ

ብሔራዊ የማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፻፮/፲፱፻፹፮ እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፤

፩· አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሠርዟል።

፪· አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል ፤

"፪) ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።"

### PROCLAMATION NO. 145/1998

### A PROCLAMATION TO AMEND THE NATIONAL FERTILIZER INDUSTRY AGENCY ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to further amend the National Fertilizer Industry Agency Establishment Proclamation,

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "National Fertilizer Industry Agency Establishment (Amendment) Proclamation No. 145/1998."

2. *Amendment*

The National Fertilizer Industry Agency establishment Proclamation number 106/1994 is further amended as follows:

1) Sub-Article (4) of Article 2 of the Proclamation is hereby deleted.
2) Sub-Article (2) of Article 3 of the Proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Sub-Article (2).
   "2) The Agency shall be accountable to the Prime Minister."

፫· የአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፱) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፱) ተተክቷል፡

"፱) የኤጀንሲውን ዓመታዊ ሪፖርት ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ያቀርባል።"

፬· በአንቀጽ ፰ ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፲ ተጨምሯል፡

"፲) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል የድርጅቱን ሙያተኛ ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል፡ የቅጥርና የአስተዳደር መመሪያ ያወጣል፡ መመሪያውንም ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ ያስጸድቃል፡ የመመሪያውን አፈጻጸም ይከታተላል።"

፭· የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ተሠርዟል።

፮· አንቀጽ ፲፪፡ ፲፫፡ ፲፬፡ ፲፭ እና ፲፮ ቁጥራቸው ተሸጋሽጎ እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፲፩፡ ፲፪፡ ፲፫፡ ፲፬ እና ፲፭ ሆነዋል።

፯· በአንቀጽ ፲፩/፩/ የመጀመሪያ ዓረፍተ ነገር ውስጥ "...በየሦስት ወሩ..." የሚለው "...በየወሩ..." በሚል ተተክቷል፡

፰· በአንቀጽ ፲፪ ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፡

"፭ በርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ሙያተኛ ሠራተኞች ይቀጥራል፡ ያስተዳድራል ፡ ደመወዝና አበላቸውንም ይወስናል፡ የድርጅቱን ሌሎች ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፡ ያስተዳድራል።"

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከታህሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

3) Sub-Article(9) of Article 8 of the Proclamation is hereby deleted and replaced by the following new sub-Article(9):

"9) Submit the annual report of the Agency to the Prime Minster's Office."

4) The following new sub-Article 10 is hereby added under Article 8:

"10) Following the basic principles of the federal civil service laws issue directives, regarding the salary scales, employment and administration of professional employees of the Agency, and follow up the implementation of same upon approval by the Council of Ministers."

5) Article 11 of the Proclamation is hereby deleted.

6) Articles 12, 13, 14, 15 and 16 are renumbered as Articles 11, 12, 13, 14 and 15 respectively.

7) The phrase "...every three months..." in the first sentence of Article 11(1) is hereby deleted and replaced by the phrase "...every month..."

8) The following new sub-Article (5) is hereby added under Article 12 of the proclamation:

"5) Employ and administer professional personnels of the Agency in accordance with directives approved by the Board, determine their salary and allowances, and other employees in accordance with the federal civil service law."

3. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 15th day of December, 1998.

Done at Addis Ababa, this 15thday of December, 1998.

NEGASO GIDADA(DR)

PRESIDENT OF THE FEDERAL

DEMOCRATIC REPPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE